“ምን ልርዳህ?”

“መልካም ፡ ቅድም ለሚስተር ሼሪቶስ እንዳስረዳሁት አንድ የዕቃ ማጓጓዣ መርከብ ለመኮናተር ፈልጌ ነበር ። በማርሴሊስ ፋብሪካ እንዳለኝ ታውቃለህ አይደል? የተወሰኑ ከባድ ማሽነሪዎችን ወደዩናይትድ ስቴትስ ለማጓጓዝ እፈልጋለሁ ። እኔና አንተ ለመስማማት የምንችል ከሆነ ወደፊትም ብዙ ሥራዎችን ላመጣልህ እችላለሁ ።”

ስፒሮስ ላምብሩ ወደኋላው ተለጥጦ ከፊትለፊቱ ያለውን ሰው በትኩረት ያጠናል ።

“አንተ እንዲጫንልህ የፈለከው ዕቃ ይሄ ብቻ ነው? ሚስተር ሪዞሊ ።”

ቶኒ ሪዞሊ ግንባሩን ኮስተር በማድረግ “ምን አልክ ? አልገባኝም ።”

“የገባህ ይመስለኛል” አለው ላምብሩ ። “መርከቤ ለአንተ አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም ።”

“ለምን ? ምንድነው የምትናገረው?”

“ስለሱሰኛ እንክብሎች ማለቴ ነው ሚስተር ሪዞሊ ። አንተ ሱስ የሚያሲዙ እንክብሎች ነጋዴ ነህ ።”

የሪዞሊ ዓይኖች ጠበቡ ።“እብድነህ መሰለኝ ! ብዙ ሐሜቶች ስትሰማ ቆይተሃል ማለት ነው ።”

ነገሩ ከሐሜትም በላይ ነው ። ስፒሮስ ላምብሩ ስለሰውዬው ደህና አድርጎ አጥንቷል ። ቶኒ ሪዞሊ በአውሮጳ ውስጥ ዕፅ የሚያሲዙ እንክብሎች በሥውር ከሚነግዱ እውቅ ሰዎች መካከል አንዱ ነው ። ቶኒ ሪዞሊ የማፊያ አባል ነው ። ዛሬ ግን እንኳን ድርጅቱ ቃሉም ጭምር እየጠፋ በመምጣቱ ዕቃውን ለማጓጓዝ ችግር አጋጥሞታል ። ከላምብሩ ጋር የተለየ ስምምነት ለማድረግ የጓጓውም ለዚሁ ነበር ።

“ሌላ ቦታ መሄድ ያለብህ ይመስለኛል ።”

ቶኒ ሪዞሊ ዓይኑ እንደፈዘዘ እዚያው እተቀመጠበት ትኩር ብሎ ላምብሩን እያየ ቀረ ። በመጨረሻም ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። “መልካም” ሲል ከኪሱ አድራሻው የተፃፈበትን ካርድ አውጥቶ ላምብሩ ጠረጴዛ ላይ ወረወረ ። “አሳብህን የምትቀይር ከሆነ በዚህ አድራሻ ልታገኘኝ ትችላለህ ።” ተነስቶ ቆም ካለ በኋላ ወጥቶ ሄደ ።

ስፒሮስ ላምብሩ ካርዱን አንስቶ ሲያነብ “አንቶኒ ሪዞሊ አስመጪና ላኪ” የሚል ተጽፎበታል ። ዝቅ ብሎ በአቴንስ የሚገኝ



የአንድ ሆቴል አድራሻና የስልክ ቁጥር ሠፍሯል ።

ኒኮስ ሼሪቶስ በዚያው ቢሮ ውስጥ ተቀምጦ ዓይኑን አፍጥጦ የሁለቱንም ውይይት በጥሞና ይከታተል ነበር ። ቶኒ ሪዞሊ ወጥቶ ሲሄድ “በእርግጥ የሱስ…”

“አዎ ፡ ሚስተር ሪዞሊ ሄሮይን ይነግዳል ። ባንዱ መርከብ ላይ እንኳን ጭነንለት ብንገኝ መንግሥት መርከቦቻችንን በሙሉ ከትራንስፖርቱ የንግድ ዓለም ያግድብናል ።”

ቶኒ ሪዞሊ ከላምብሩ ቢሮ የወጣው በጣም ተበሳጭቶ ነው ። ‘ያ ደደብ ግሪክ እንደአንድ ገልቱ ገበሬ አደረገኝ አይደል! ስለሱስ አስያዥ መድኃኒቶቹ እንዴት ለማወቅ ቻለ? ወይኔ! ይህን አሥር ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ትልቅ ጭነት እንዴት አድርጌ ነው ኒውዮርክ ለማድረስ የምችለው ? የሚከታተሉን ኃይሎች ደግሞ በመላ አቴንስ ውስጥ ተሰራጭተው አስጨንቀውናል ። ወደ ሲሲሊ ስልክ መደወል አለብኝ ’ አለ በአሳቡ ።

ቶኒ ሪዞሊ ከዚህ በፊት ለጭነት ጠይቆ እምቢ ያለው የለም ። እዚህም እምቢ እባላለሁ ብሎ ፍፁም አልጠረጠረም ። እራሱን ዘለዓለም እንደአሸናፊ ነበር የሚቆጥረው ።

ያደገው ኒውዮርክ ውስጥ ከማንሃታን በስተምዕራብ በኤይትዝ ጐዳናና በሀድሰን ወንዝ መካከል በምትገኘው ሄልስ ኪችን በምትባል ሥፍራ ነው ። በስተሰሜንና በስተደቡብ በቱዌንቲ ሰርድና ፡ ፊፍቲ ናይንዝ ጐዳናዎች ትዋሰናለች ። ሄልስ ኪችን በከተማ መሐል የምትገኝ አነስተኛ ከተማ ናት ለማለት ይቻላል ። በቡድን በቡድን የተደራጁ ፡ ጐፐርስ ፡ ፓርሎር ሞብ ፡ ጐነላስ ፡ ሮድስ ጋንግ የሚል ስያሜ ለእራሳቸው የሰጡ ዱርዬዎች የበላይነት የሰፈነባት ናት ። በከተማዋ ውስጥ በመቶ ዶላር ውል ሰው ማስገደል ይቻላል ።

በሄልስ ኪችን የሚገኙ ነዋሪዎች ፅዳት በሌላቸው ቤቶች የሚኖሩ ሲሆኑ በአይጥ በቅማልና በሌሎች ተባዮች የተወረሩ ናቸው ። የገላ መታጠቢያ ሥፍራዎች የሉባትም ። ወጣቶች ገላቸውን የሚታጠቡት ከሀድሰን ወንዝ ዳርቻ ሆነው ነው ። ከፋብሪካ ተለቆ በሄልስ ኪችን ጐዳናዎች ሥር በቱቦ የሚጓዘው ቆሻሻ ፡ ሞተው የጠነቡ እንስሳት ፡ አካላቸው የፈረሰ ድመቶች ፡ የሸተቱ ውሾች ሁሉ ተጠራርገው የሚገቡት ከዚሁ ወንዝ ውስጥ ነው ።

# ምዕራፍ ሰባት

በአቴንስ ከተማ ውስጥ የሚገኘው የአርሳኪዮን ፍርድ ቤት ግራጫማው የድንጋይ ሕንጻ በጣም ትልቅ ነው ። ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ የዩኒቨርስቲና የስትራይን ጐዳናዎችን ብዙ ቦታ አካብቦ ይዟል ። በሕንጻው ውስጥ ከሚገኙት 30 ችሎቶች መካከል የወንጀል ክስ የሚታይባቸው ሦስቱ ብቻ ናቸው ። የእነኚህም ችሎቶች ቁጥር 21 ፡ 30 እና 33 ነው ።

የአናስታሺያ ሳቫላስን በነፍስ ግድያ ወንጀል መከሰስ ለመከታተል ቁጥሩ በዛ ያለ ሕዝብ በመምጣቱ ጉዳይዋ በቁጥር 33 ችሎት ውስጥ እንዲታይ ተደረገ ። ክፍሉ 40 ጫማ ስፋትና 300 ጫማ ርዝመት አለው ። መቀመጫዎቹ በሦስት ረድፍ የተደረደሩ ሲሆኑ በእያንዳንዱ መቀመጫ መካከል የስድስት ጫማ ርቀት አለ ። በእያንዳንዱ ረድፍም ዘጠኝ አግዳሚ ወንበሮች ተደርድረዋል ። ፊት ለፊት ሦስቱ ዳኞች የሚሰየሙበት ከፍ ያለ ሥፍራ አለ ።

ከዳኞቹ ፊት ለፊት ምስክሮች ቆመው ቃል የሚሰጡበት ቦታም ተዘጋጅቷል ። ራቅ ብለው በግድግዳው ጥግ ከተራ ሰዎች ተመርጠው የፍርድ አሳብ የሚሰጡ የ10 ሰዎች መቀመጫ ሥፍራም ይታያል ። ከተከሳሹ ማቆሚያ ሳጥን ፊት ለፊት የጠበቃው መቆሚያ ቦታም ይገኛል።

የግድያ ወንጀሉ ክስ እራሱ በጣም አስደናቂ ጉዳይ ሆኖ መሰንበቱ ብቻ ሳይሆን ለተከሳሾቹ የቆመው ጠበቃ ናፖሊዮን ቾታስ በዓለም ውስጥ በወንጀል ክስ ጥብቅና የታወቀ መሆኑም ጭምር ነው ። ቾታስ ባለፉት ጊዜያት በጣም አስደናቂ ውጤቶችን ያስመዘገበ ሰው ነው ። የሚጠይቀው ክፍያ ወደ ሚሊዮን ዶላር አካባቢ እንደሚጠጋ ሲናፈስ ይሰማል ። ናፖሊዮን ቾታስ ቀጠን ያለ ኮስማና ሲሆን ኮስታራ ነው ። በአለባበስ ረገድ እራሱን የማይጠብቅ ቢሆንም ዝርክርክ መሳይነቱ በሰዎች እምነት



ላይ ምንም ተፅዕኖ አያደርግም ። በጣም የሚያስደንቅ ብልህና አርቆ አስተዋይ ነውና ።

ናፖሊዮን ቾታስ ፣ የወንጀል ክስ የተመሰረተባት ሴትዮ ጠበቃ ሆኖ በመቅረቡ ዜና ማሰራጫዎች በጉዳዩ ላይ አስተያየቶችንና ትችቶችን ሰንዝረዋል ። በአንድ በኩል ሊረታ የሚችልበት ምንም መንገድ እንደሌለ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ቾታስ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚረታበት ወቅት መቃረቡ በብዙዎቹ ተወስቷል ።

ሕግ አስከባሪው ፒተር ዲሞኒዴስና ቾታስ ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ ከችሎት ቀርበው ተፋልመዋል ። የቾታስ የክርክር ስልትና ጥበብ ዲሞኒዴስን የሚያስደንቀው ቢሆንም ይህንኑ እምነቱን ይፋ አያወጣውም። ይሁንና የአሁን ክርክር ዲሞኒዴስን ብዙም እንደማያስጨንቀው አውቋል ። እስካሁን ከቀረቡት የወንጀል ክሶች መካከል ቶሎ ውሳኔ የሚሰጥበት ቀላል ነገር ቢኖር የአናስታሺያ ጉዳይ ነው ። ወንጀሉ ግልጽ ወጥቶ ይታያል ። የተዋበችዋ ወጣት አናስታሺያ ሳቫላስ በሰላሳ ዓመት ታላቋ የሆነውን ባለፀጋ ጆርጅ ሳቫላስን አግብታ ነበር ። አናስታሺያ ዮሴፍ ፓፓስ ከተባለው ወጣት ሾፌራቸው ጋር አንሶላ በመጋፈፍ ባሏ ሊፈታት እንደዛተባትና እንዲሁም ከውርስ ኑዛዜ ሰነድ ስሟን እንደፋቀ ምስክሮች ተናግረዋል ። ግድያው በተፈጸመበት ማታ የቤት ሠራተኞቹን አሰናብታ ለባሏ እራቷ እራት አሠናዳች ። ጆርጅ ሳቫላስን ኃይለኛ ጉንፋን ይዞት ስለነበር በእራት ላይ በጣም አሳለው ። ሚስቱ የሳል መድኃኒቱን ብልቃጥ አመጣችለትና ሳቫላስ ከመድኃኒቱ ላይ ጠጥቶ ወዲያውኑ ሞተ ።

ያለቀለት ክስ ።

ተመልካቹ ሕዝብ ገና በጠዋቱ ችሎት ቁጥር 33ን ሞልቶታል ። አናስታሺያ ሳቫላስ ጥቁር ጉርድ ቀሚስና ሸሚዝ ለብሳ ከተከሳሽ ወንበር ላይ ተቀምጣለች ። ምንም ዓይነት ጌጣጌጥ ያላጠለቀች ሲሆን ፊቷንም እምብዛም አልተኳኳለችም ።

ሕግ አስከባሪው ፒተር ዲሞኒዴስ ለፍርድ ቤቱ ክሱን አሰማ ።

“ክቡራትና ክቡራን ፡ ለወንጀል ክስ ውሳኔ ለማግኘት አንዳንድ ጊዜ ከሦስት እስከ አራት ወራት ይፈጃል ። ይህ ጉዳይ ግን ያን ያህል ጊዜ ይወስዳል የሚል ሥጋት እንዲያሳድርባችሁ አይገባም ። የሚቀርበውን ክስ መረጃ በምታዩበትና በምትሰሙበት ወቅት ፡ እርግጠኛ ነኝ የአንደኛ

"ሥራው ተስማምቶህ ነበር ፡ ሚስተር ፓፓስ?"

"ደህና ነበር መሰለኝ"

"ጥሩ ደመወዝ ይከፈልህ ነበር?"

"አዎ"

"ታድያ ሥራው ደህና ብቻ ሳይሆን በጣም ጥሩ ነው አትልም? ማለት ሌላ ተጨማሪ ጥቅም አልነበረውም? ዘወትር ከሚስስ ሳቫላስ ጋርስ ወሲብ አትፈጽምም ነበር?"

ጆሴፍ ፓፓስ አሁንም እርዳታ ፍለጋ ወደናፖሊዮን ቾታስ ተመለከተ ። ሆኖም ምንም አላገኘም ።

"እኔ … አዎ ጌታዬ ይመስለኛል ።"

ፒተር ዲሞኒዴስ ቆጣ አለና "ይመስልሀል? ቃለ መሐላ ፈጽመሃል እኮ ። አብረሃት ተኝተህ ታወቃለህ ወይስ አታውቅም?"

ፓፓስ እየተሽኮረመመ "አዎ ግንኙነት ነበረን" አለ ።

"ባለቤቷ ቀጥሮ እያሠራህ ፡ ጥሩ ደሞዝ እየከፈለህ እንዲሁም ውብ መኖሪያ ሰጥቶህ?"

"አዎ ጌታዬ ።"

"በሹልክታ ከሚስቱ ጋር የፍትወት ግንኙነት እያደርግክ የሚስተር ሳቫላስን ገንዘብ ስትቀበል አይቀፍህም ነበር?"

"የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ብቻ አልነበረም"

ፒተር ዲሞኒዴስ ወጥመዱን በጥንቃቄ እያዘጋጀ "የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ብቻ አልነበረም? እንዲህ ስትል ምን ማለትህ ነው? አባባልህ ግልጽ አልሆነልኝም ።"

"ማለቴ እኔና አናስታሺያ ለመጋባትም አቅደን ነበር ።"

በችሎቱ ውስጥ የነበረው ሰው ሁሉ ተገርሞ ሲያጉረመርም የፍርድ አሳብ ሰጪዎች ወደተከሳሿ ይመለከቱ ነበር ።

"የጋብቻ አሳቡን ያቀረብከው አንተ ነህ ወይንስ ሚስስ ሳቫላስ?"

"ሁለታችንም ፈልገነው ነበር ።"

"መጀመሪያ አሳብ ያቀረበው ማነው?"

"እንደሚመስለኝ እርሷ ናት" አለና አናስታሺያ ሳቫላስን ከተቀመጠችበት ተንጠራርቶ አያት ። እሷ ግን ለእይታው ፍንከች አላለችም ።



"በእውነት ለመናገር ሚስተር ፓፓስ ግራ ገብቶኛል ። በእንዴት ዓይነት ሁኔታ እንጋባለን ብለህ ገምተህ ነበር? ሚስስ ሳቫላስ እንደሆን ባል ነበራት ። በእርጅና ምክንያት ይሞታል ብለህ? ይህ እስኪሆን የመጠበቅ እቅድ ነበረህ? ወይስ አንድ የሆነ አደጋ ቢፈጠር ብለህ? በትክክል በአእምሮህ ውስጥ የነበረው አሳብ የትኛው ነው?"

ጥያቄው በጣም አደገኛ በመሆኑ ሕግ አስከባሪውና ሦስቱም ዳኞች የተቃውሞ ቁጣ ከናፖሊዮን ቾታስ ይሰነዘራል ብለው ጠበቁ ። ሆኖም የተከሳሿ ጠበቃ አሁንም ፈዞ ተቀምጧል ። እንዲህ መሆኑ አናስታሺያ ሳቫላስንም ጭምር አሳስቧታል ።

ፒተር ዲሞኒዴስ ያገኘውን ቀዳዳ የበለጠ ለማስፋት "ጥያቄዬን አልመለስክልኝም ሚስተር ፓፓስ" አለ ።

ዮሴፍ ፓፓስ እየተቁነጠነጠ ወደጠያቂው ዞር አለ ። "ትዝ አይለኝም"

ፒተር ዲሞኒዴስ ድምጹን እያሰላ መጣ ።

"በል እኔ ትዝ እንዲልህ ልርዳህ ። እንቅፋት እንዳይሆንባት ሚስስ ሳቫላስ ባሏን ልትገድለው አቀደች ። ባለቤቷ ከኑዛዜው ውስጥ ስሟን ለመሰረዝ መወሰኑን አውቃ ነበር ። እርሷ …"

"ተቃውሞ !" ቃሉ የተወረወረው ከናፖሊዮን ቾታስ ሳይሆን ከመሐል ዳኛው ነበር ። "ለምስክሩ የቀረበው ጥያቄ ግምታዊ ምላሽን የሚጋብዝ ነው ።" ጠበቃው ዝም በማለቱ ተገርመው የመሐል ዳኛው ናፖሊዮን ቾታስን አዩት ። ሊያሸልበው ይመስል ዓይኑ ሊከደን የተቃረበው ቾታስ አግዳሚውን ወንበር ወደኋላ ተደግፎ ተዝናንቶ ተቀምጧል ። "ይቅርታ ክቡር ጌታዬ" አለ ሕግ አስከባሪው ። የተጠየቀውን በትክክል ስለሚያውቅ ግምታዊ ምላሽ እንደማይሰጠው ያውቅ ነበር ። ፒተር ዲሞኒዴስ ወደቾታስ ዞር አለና "ምስክሩ ይኸውልህ" አለው ።

ናፖሊዮን ቾታስ ከተቀመጠበት ተነሳና "አመሰግናለሁ ሚስተር ዲሞኒዴስ ጥያቄ የለኝም " አለ ።

ሦስቱ ዳኞች በጣም ተገርመው እርስ በእርስ ተያዩ ።

ከሦስቱ አንደኛው "ሚስተር ቾታስ ለዚህ ምስክር መስቀለኛ ጥያቄ ለማቅረብ ያለህ ዕድል አሁን ብቻ መሆኑን ታውቃለህ ?"

ናፖሊዮን ቾታስ በአዎንታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "አዎ ጌታዬ"

"የሰጠውን የምስክርነት ቃል በሚመለከት ጥያቄ ልታቀርብለት አትሻም ?"

ናፖሊዮን ቾታስ እጁን አወዛወዘ ።

“የለኝም ክቡር ጌታዬ ።”

ዳኛው ፈገግ አሉ ። “መልካም ፣ ሕግ አስከባሪው የሚቀጥለው ምስክሩን ሊያቀርብ ይችላል ።”

ተከታዩ ምስክር ሚሃሊስ ሃሪቶኒደስ ይባላል ። ሰውዬው መልከ መልካም ቢሆንም ዕድሜው ወደስልሳው ገደማ ነው ።

ሃሪቶኒደስ ቃለ መሐላውን እንደፈጸመ ሕግ አስከባሪው ጥያቄዎችን ያቀርብለት ጀመር ። “ሥራህ ምን እንደሆነ ለፍርድ ቤቱ ልትገልጽ ትችላለህ ?”

“አዎ ጌታዬ ፣ የሆቴል አስተዳዳሪ ነኝ።”

“የሆቴሉስ ስም ?”

“አርጎስ”

“ሆቴሉ የሚገኘው የት ነው ?”

“በኮርፉ”

“በዚህ ፍርድ ቤት ውስጥ ከሚገኙ ሰዎች በሆቴልህ አርፈው የነበሩ ካሉ እንድትነግረኝ ነው ሚስተር ሃሪቶኒደስ ።”

ሃሪቶኒደስ ዙሪያውን ተመለከተ ። “አዎ ጌታዬ ፣ እርሱና እርሷ ።”

“ምስክሩ ወደ ዮሴፍ ፓፓስና ወደ አናስታሺያ ሳቫላስ ማመልከቱ በደንብ ተረጋግጦ ይመዝገብልኝ ።” ወደምስክሩ መልሶ ዞረና “በሆቴልህ ውስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ ሠፍረዋል ?”

“አዎ ጌታዬ ። ብዙ ጊዜ መጥተዋል ።”

“እና ሌሊቱን አብረው በአንድ ክፍል ውስጥ ያሳልፉ ነበር ?”

“አዎ ጌታዬ ። ብዙ ጊዜ ቅዳሜና እሁድ ይመጡ ነበር ።”

“አመሰግናለሁ ሚስተር ሃሪቶኒደስ” አለና ዞር ብሎ ወደናፖሊዮን ቾታስ በመመልከት “ምስክሩ ይኸውልህ” አለው ።

“ጥያቄ የለኝም ።”

የመሐል ዳኛው የግራና የቀኝ ዳኞችን ተራ በተራ ካዩ በኋላ ሦስቱም ለጥቂት ጊዜ ተንሾካሾኩ ።

የመሐል ዳኛው ወደናፖሊዮን ቾታስ እየተመለከቱ “ለዚህኛውም ምስክር ምንም ጥያቄ የለህም ሚስተር ቾታስ?”

“ምንም ፡ ክቡር ጌታዬ የምስክሩ ቃል ትክክል ነው ። ሆቴሉ በጣም ጥሩ ስለሆነ እኔም አርፌበት ነበር ።”



ዳኛው ናፖሊዮን ቾታስን ረዘም ላለ ጊዜ ትኩር ብለው አዩትና ወደ ሕግ አስከባሪው ተመለሱ ። “የሚቀጥለው ምስክር ሊቀርብ ይችላል” አሉ ።

ቀጥሎ የተጠራው ዶክተር ቫሲሊስ ፍራንጂስኮስ ነው ።

ከቁመቱ ረዘም ያለ ፣ ደንዳና ቁመና ያለው ሰው ተነሳና ወደምስክሮች መቆሚያ ሳጥን ገባ ። ቃለ መሐላም ፈጸመ ።

“ዶክተር ፍራንጂስኮስ ፣ በምን ዓይነት የሕክምና ሥራ ላይ እንደተሰማራህ ለፍርድ ቤቱ ብትገልጽ ?”

“የጠቅላላ ሕክምና ዶክተር”

“ይህ ሥራ ከቤተሰብ ዶክተርነት ጋር እኩል ደረጃ አለው ?”

“ሙያውና ደረጃው ያው አንድ ነው ፤ መጠሪያው ተለያየ እንጂ ።”

“ዶክተር ፡ በሥራ ላይ የቆየኸው ለምን ያህል ጊዜ ነው ?”

“ለሰላሳ ዓመታት ያህል”

“የሕክምና ፍቃድ በመንግሥት ተሰጥቶሃል ?”

“እንዴታ”

“ዶክተር ፍራንጂስኮስ ፣ ጆርጅ ሳቫላስን ታክመው ነበር ?”

“እዎ ነበረ ።”

“ለምን ያህል ጊዜ ?”

“ከአሥር ዓመታት በላይ ።”

“ሚስተር ሳቫላስን ልዩ የሆነ በሽታ ይዞት አክመኸው ታውቃለህ?”

“አዎ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደእኔ የመጣው የደም ብዛት ሕመም በያዘው ጊዜ ነበር ።”

“ሕክምና አደረግክለት ?”

“አዎ”

“ከዚያ በኋላስ አግኝተኸው ታውቃለህ ?”

“አዎ ። አንዴ ብሮንካይተስ ፣ ሌላ ጊዜ የጉበት በሽታ ይዞት አክሜዋለሁ። ከዚህ የከፋ በሽታ ግን እጋጥሞት አያውቅም ።”

“ለመጨረሻ ጊዜ ሚስተር ሳቫላስ አንተ ዘንድ የመጣው መቼ ነው?”

“ባለፈው ዓመት በዲሴምበር ወር”

“ከመሞቱ ጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ ማለት ነው ?”

ከሚስተር ሳቫላስ ጋር የፍቅር ግንኙነት ሊኖራት ይችል ይሆናል ። አንድ ጥልቅ ስሜት ወይም ፍላጐት ከውስጥ ሳይኖራት ለአንድ ሰው ለሃያ አምስት ዓመታት በተከታታይ የምትሠራበት ምክንያት አይኖርም ። በዚህም የተነሳ አናስታሺያ ሳቫላስን ትጠላታለች ለማለት እንችላለን ። ይህንንም ከአነጋገሯ ለማወቅ ትችላላችሁ” ሲል ጉሮሮውን ጠረገ ።

“ተከሳሿ ባሏን በጣም ትወደው ስለነበር ትዳሯ እንዳይፈርስ ትጥራለች እንበል ። ከዚህ በላይ አንዲት ሴት ለወንድ ፍቅሯን የምታሳየው እንዴት ነው ? አንዱ መንገድ እንደሚመስለኝ ምግብ በማዘጋጀት ነው ። ይህ የፍቅር መግለጫ ምልክት አይደለም ነው የምትሉት ? እኔ በበኩሌ ነው እላለሁ ።” አለና አሁንም ዞር ብሎ ብልቃጡን ተመለከተ ። “ሌላው መግለጫ መንገድ ደግሞ ባልዬው በሚታመምበት ወቅት እንክብካቤ ማድረግ አይደለምን ? በበሽታ ጊዜ አለመራቅ !”

በግርግዳው ላይ የተሰቀለው ሰዓት ስድስት ሊል አንድ ደቂቃ መቅረቱን ያመለክታል ።

“ክቡራትና ክቡራን ፤ ፍርድ ቤቱ ገና ሥራውን እንደጀመረ የዚህችን ሴት ፊት እንድትመለከቱ ጠይቄአችሁ ነበር ። ፊቷ የነፍሰ ገዳይ ፊት አይመስልም ። ዓይኖቿም የነፍሰ ገዳይ ዓይን አይደሉም ።”

አሥሩ ሰዎች ተከሳሿን ሲመለከቱ ፒተር ዲሞኒዴስ ትኩር ብሎ ያያቸው ነበር ። እንዲህ ዓይነቱን የጥላቻ አመለካከት ከእነዚህ ሰዎች ፊት ላይ ተመልክቶ አያውቅም ። አሁን የሰዎቹን ስሜት እየተቆጣጠረ መምጣቱ ገባው ።

“ሕጉ በጣም ግልጽ ያለ ነው ክቡራትና ክቡራን ። ወንጀለኛው ጥፋተኛ ሆኖ የሚገኘው የተከሳሽ ጥፋተኛነት ሲረጋገጥ መሆኑን የተከበሩ ዳኞች ሊገልጹላችሁ ይችላሉ ። ሳይረጋገጥ የሚወሰን ነገር የለም።”

ናፖሊዮን ቾታስ ንግግሩን ቀጥሎ በመሐል እንደገና አሳለውና ከኪሱ መሐረብ አውጥቶ አፉን ሸፈነ ። የሳሉ መድኃኒት ከሸንጐው አጠገብ ወደተቀመጠበት ጠረጴዛ ሄደ ።

“በጥሞና ብትመለከቱት ሕግ አስከባሪው ያቀረበው ተጨባጭ ማስረጃ የለም ። ሚስስ ሳቫላስ ለባለቤቷ ሰጠች ከሚባለው ከዚህ መድኃኒት በቀር በእውነት ለመናገር ምንም አሳማኝ ነገር አልቀረበም ።”



ተናግሮ እንደጨረሰ ሳል አጣደፈው ። ሳያውቀው የሳል መድኃኒቱን አንስቶ ወደአፉ በማቅረብ ጠጣው ። በፍርድ ቤቱ ውስጥ የነበረው ሰው ሁሉ በድንጋጤ አፍጥጦ አየው ። ተመልካቹ ተሸበረ ። ፍርድ ቤቱም በሁካታ ተሞጠ ።

የመሐል ዳኛው በመገረም “ሚስተር ቾታስ …” አሉ ።

ናፖሊዮን ቾታስ እንደገና መድኃኒቱን ተጐነጨው ። “ክቡር ጌታዬ ሕግ አስከባሪው በፍርድ ቤቱ እየቀለደ ነው ። ጆርጅ ሳቫላስ የተገደለው በዚህች ሴት እጅ አይደለም ። የመከላከያ አሳቤን በዚህ አጠቃልላለሁ ።”

ሰዓቱ ልክ ስድስት ሰዓት መሆኑን በደወል አበሰረ ። ዘቡም ፈጠን ባለ እርምጃ ወደ መሐል ዳኛው ጆሮ ተጠግቶ አንሾካሾከ ።

የመሐል ዳኛው በመዶሻ ጠረጴዛውን መታ መታ አደረጉ ። “ሥነ ሥርዓት ፡ ሥነ ሥርዓት ፣ አሁን የእረፍት መውጫ ጊዜ ነው ። ሸንጐዎችም ተሰናብተዋል ። ከውሳኔ ነጥብ ላይ ደርሰው ይመለሳሉ ። ፍርድ ቤቱም በስምንት ሰዓት ሥራውን ይጀምራል ።” አሉ ።

ፒተር ዲሞኒዴስ እዚያው በቆመበት ፈዞ ቀረ ። ብልቃጡ ተቀይሮ ይሆን ? ግን እንዴት ሊሆን ይችላል ? በኤግዚቢትነት በደንብ ሲጠበቅ የነበረ ነው ። ምናልባት አስከሬኑን የመረመሩት ሰዎች የተሳሳተ ውጤት ልከው ይሆን ? ዲሞኒዴስ ረዳቱን ሊያነጋግር ዞር ብሎ ሲመለስ ናፖሊዮን ቾታስን በዓይን ፈልጎ አጣው ። እርሱ የለም ወጥቶ ሄዷል ።

በስምንት ሰዓት ችሎቱ እንደገና ሲሰየም የሸንጐው አባላት አንድ በአንድ ገብተው ወንበራቸው ላይ ተቀመጡ ። ናፖሊዮን ቾታስ ግን የት እንደደረሰ አልታወቀም ።

‘ያ የውሻ ልጅ ሳይሞት አልቀረም’ አለ ፒተር ዲሞኒዴስ በአሳቡ ።

ስለእርሱው በማውጠንጠን ላይ እያለ ናፖሊዮን ቾታስ ብቅ አለ ። በተመልካቹ መሐል አልፎ ወደመቀመጫው ሲጓዝ ሁሉም ሰው ትኩር ብሎ እንደጉድ ተመለከተው ።

የመሐል ዳኛው “የተከበራችሁ የሸንጐ አባላት ከውሳኔ ላይ ደረሳችሁ ?” ብለው ጠየቁ ። የሸንጐው ሰብሳቢ ተነሳና “አዎ ደርሰናል ክቡር ጌታዬ ። ተከሳሿ ጥፋተኛ ሆና አላገኘናትም ።”

በክፍሉ ውስጥ የነበረው ተመልካች ጭብጨባውን አቀለጠው ።

የፒተር ዲሞኒዴስ ፊት ደም ለበሰ ። ‘ይህ ደደብ እንደገና ጉድ አደረገኝ አይደል?’ አለ በልቡ ። ቀና ብሎ ሲያየው ናፖሊዮን ቾታስ በፈገግታ ይመለከተው ነበር ።

ትሪትሲስ ተቋም ባልደረባ ከካፒኒካሪአ ቤተክርስቲያን ሲወጣ ገጭታው ባመለጠች አንዲት መኪና አደጋ ሕይወቱ አለፈ ። የዓይን ምስክሮች መኪናዋ ታርጋ የሌላት ጥቁር ሊሞሲን መሆኗን ገልፀዋል ። በኖኤሌ ፖጂና በላሪ ዶግላስ ላይ ተከፍቶ በነበረው የግድያ ወንጀል ክስ ሚስተር ስታቭሮስ ለላሪ ዶግላስ ጥብቅና ቆሞ የነበረ ዝነኛ ሰው ነው ...”

ናፖሊዮን ቾታስ ማንበብ አቆመ ። ቁርሱን ረሳውና እተቀመጠበት ረዞ ቀረ ። አደጋ ። ‘እውነት አደጋ ነው ?’ አለ በልቡ ። ቀደም ሲል ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ምንም የሚያሳስብ ነገር እንደሌለ ገልጦለት ነበር። ግን ብዙ ሰዎች ዴሚሪስ ላይ ላዩን በሚያሳያቸው ገጽታ ይታለላሉ ።

ቾታስ ስልኩን አንስቶ ለኮንስታንቲን ዴሚሪስ ሲደውል ፀሐፊዋም አገናኘችው ።

“የዛሬ ጠዋት ጋዜጦችን አንብበሃል?” ብሎ ቾታስ ጠየቀ ።

“የለም አላነበብኩም ፤ ምነው?”

“ፍሬዴሪክ ስታቭሮስ ሞተ እኮ”

“ምን ?” አለ እንደመደንገጥ ብሎ ።

“ምንድነው የምትናገረው ?”

“በመኪና ትላንትና ማታ ተገጭቶ ሞተ ። መኪናዋ አምልጣለች ።”

“አቤት አምላኬ ! በጣም የሚያሳዝን ነው ። ሊአን ፥ ሾፌሩን ይዘውታል?”

“እስካሁን አልተያዘም ።”

“ክትትሉን እንዲያፋጥኑት በፖሊሶቹ ላይ ግፊት ማድረግ ይኖርብ ኛል ። በዛሬ ጊዜኮ ምንም አልሆንም ማለት አይቻልም ። በነገራችን ላይ ሐሙስ አብረን እራት ብንበላ ይመችሃል?”

“መልካም”

“ጥብቅ ቀጠሮ ነው ።”

ናፖሊዮን ቾታስ የሰውን ንግግር አብጠርጥሮ የመረዳት ችሎታ አለው ። “ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በአደጋው አዝኗል ። በስታቭሮስ ግድያ ውስጥ እጁ የለበትም” ሲል ደመደመ ።

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ናፖሊዮን ቾታስ መኪናውን እየነዳ ቢሮው ከሚገኘው የመኪና ማቆሚያ ወስዶ አቆማት ። ከመኪናው ወርዶ ወደ አሳንሰሩ እንዳመራ አንድ ወጣት ጨለምለም ካለ ሥፍራ ብቅ



አለበት።

“ክብሪት አለህ ?”

የቾታስ አእምሮ የማስጠንቀቂያ ደወል ደወለ ። ወጣቱ በመኪና ማቆሚያው ሥፍራ ታይቶ የማይታወቅ ነው ።

“አዎ” አለና ቾታስ ባንጠለጠለው ቦርሳ ከመቅጽበት ሰውዬውን ፊቱ ላይ መታው ።

ወጣቱ በሲቃ ጮኸ ። “አንተ የውሻ ልጅ !” አለና ከኪሱ ውስጥ ድምጽ የሌለው ሽጉጥ አወጣ ።

“እንዴ ! አንተ ሰው ምን እያደረግህ ነው ?” እያለ የደንብ ልብስ የለበሰ ዘብ ወደ እነርሱ ገሠገሠ ። እንግዳው ወጣት እንደማመንታት ካለ በኋላ ወደበሩ ሮጠ ። ዘቡም ከቾታስ አጠገብ ደረሰ ። “ደህና ነህ ሚስተር ቾታስ ?”

“እ...አዎ” የናፖሊዮን ቾታስ ትንፋሽ ቁርጥ ቁርጥ አለ ። “ደህና ነኝ ።”

“ምን ሲያደርግ አገኘኸው ?”

“ምን አውቄ ?” አለ ናፖሊዮን ቾታስ በርጋታ ።

“አጋጣሚ ሊሆን ይችላል” አለ ቾታስ ወንበሩ ላይ እንደተቀመጠ ።

“ምናልባት ሰውዬው ስርቆት ሊፈጽም አስቦ ይሆናል ። ግን ሰዎችን ለመዝረፍ ድምጽ የሌለው ሽጉጥ መያዝ አያስፈልግም ። የለም ፡ ሆን ብሎ ሊገድለኝ ነው የመጣው ።” ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የፍሬዴሪክ ስታቭሮስን መገደል ሲሰማ የደነገጠ እንደመሰለ ሁሉ ይህኛውም ቢነገረው የደነገጠ እንደሚመስል ቾታስ ተንብየዋል ። ‘መጠርጠር ነበረብኝ’ አለ ቾታስ በአሳቡ ። ‘ዴሚሪስ የሚጠነቀቅ ሰው ነው ። የሚያከናውነውን ተግባር በግላጭ የሚፈጽም አይደለም ።’

የናፖሊዮን ቾታስ ፀሐፊ ድምጽ ከኢንተርኮሙ ውስጥ ተሰማ ። “ሚስተር ቾታስ በሰላሳ ደቂቃ ውስጥ ፍርድ ቤት መገኘት አለብህ ።”

ዛሬ አንድን የግድያ ወንጀል ክስ የውሳኔ አሳብ እንዲያቀርብ የሚጠበቅበት ነው ። ሆኖም ቾታስ በመደንገጡ ወደፍርድ ቤት ለመሄድ አልፈለገም ። “ለዳኛው ደውዪና መታመሜን ንገሪያቸው ። አንድ የሥራ ባልደረባዬ እኔን ተክቶ እንዲገኝ አድርጊ ። የስልክ ጥሪ ይብቃ ።”

ከጠረጴዛው ኪስ ውስጥ ቴፕሪኮርደር አወጣና ተቀምጦ በሀሳብ

በሚቀጥለው ቀን የሕግ አስከባሪው ማልዶ ከኮንስታንቲን ዴሚሪስ ቤት ደረሰ ። ሠራተኛው ዴሚሪስ ወደሚገኝበት ወደጥናት ክፍሉ አስገባቸው ። "እንደምን አደርክ ፒተር" አለ ዴሚሪስ ። "በመምጣትህ አመሰግናለሁ ። ያንን አመጣኸው ?"

"አዎ ጌታዬ" አለና ናፖሊዮን ቾታስ በአደራ መልክ ሰጥቶት የነበረውን የታሸገ ፖስታ ሰጠው ። "ይህ እርሶ ዘንድ እንዲቆይ ይፈልጉ እንደሆነ ብዬ ነው ።"

"በጣም አስበህልኛል ፒተር ። ቁርስ ይቅረብልህ !"

"ኤፋሪስቶ ፣ ደስ ይለኛል ሚስተር ዴሚሪስ ።"

"ኮስታ ብለህ ጥራኝ ። ለብዙ ጊዜ ዓይኔን ጥዬብህ ቆይቻለሁ ። ፒተር ለወደፊት ጥሩ ዕድል እንደሚኖርህ እገምታለሁ ። በድርጅቴ ውስጥ ለአንተ የሚስማማ የሥራ ቦታ አግኝቼልሃለሁ ። ፈቃደኛ ነህ ?"

ፒተር ዲሞኒዴስ ፈገግ አለ ። "አዎ ኮስታ በጣም ደስ ይለኛል ።"

"ጥሩ ፣ በቁርስ ላይ እንወያይበታለን ።"



# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ለንደን

ካተሪንና ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በሳምንት አንዴ በስልክ ይገናኛሉ ፤ ይህም እንደልማድ ሆኗል ። ስጦታ በየጊዜው ይልክላታል ፣ ተቃውሞዋን ስታሰማ ለሥራዋ አድናቆት ለመግለጽ የሚሰጣት አነስተኛ ስጦታ መሆኑን ይነግራታል ። የባክስተርን ጉዳይ በጥሩ ሁኔታ መያዝሽን ኤቨሊን ነግራኛለች ወይም ያፈለቅሽው አሳብ በማጓጓዣ ተግባራችን ላይ ብዙ ገንዘብ ከመክፈል እንዳዳነን ከኤቨሊን ሰምቻለሁ ይላታል ። እውነትም ካተሪን ሥራዋን በጥሩ ሁኔታ በማከናወኗ ኩራት ተሰምቷታል ። በቢሮው ውስጥ ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ብዙ ነገሮች ለማሻሻል ሞክራለች ።

የድሮው የሥራ ችሎታዋን መልሳ አግኝታዋለች ። እርሷ ከመጣች ወዲህ የቢሮው ሥራ መቀላጠፉን ተረድታለች ።

"እኮራብሻለሁ " አላት ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ።

ካተሪንም ሞቅ አላት ። 'ምን ዓይነት ለሰው የሚያስብ ደግ ሰው ነው ።'

'አሁን ሥራዬን የምጀምርበት ወቅት ነው' አለ ዴሚሪስ በአሳቡ ። ስታቭሮስና ቾታስ በዘዴ ተወግደዋል ። ካለፈው ድርጊቶቼ ጋር ግንኙነት ያላት ካተሪን ብቻ ናት ። በዚህ በኩል ያለው አደጋ መጠነኛ ቢሆንም ቾታስ ከዚህ በፊት ተገንዝቦት እንደነበረው ፤ ዴሚሪስ ቀላሉን ነገር ቸል የሚል አይደለም ። 'የግድ መሄድ ስለሚኖርባት አዝናለሁ' አለ ዴሚሪስ በሀሣቡ። 'በጣም ቆንጆ ናት። ግን በመጀመሪያ ራፊና ያለው ቪላ ።'

እንዲያም ሆና ሙሉ ደስታ አታገኝም ነበር ። ኋላ ላይ ኪርክ ሬኖልድስ መጣ ።

ቢሮዋ ውስጥ ተቀምጣ እንዳለች ከቁመቱ ረዘም ያለ መልከ መልካም ሰው ከእርሷ ዘንድ ደረሰ ። “ኪርክ ሬኖልድስ እባላለሁ ። እስካሁን የት ነበርሽ?” አላት ።

“ምን አልከኝ?”

“ስጠብቅሽኮ ነበር ።”

ነገሩ እንግዲህ እንደዚህ ነበር የተጀመረው ።

አሜሪካዊው ኪርክ ሬኖልድስ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለተጠቃለሉት የኮንስታንቲን ዴሚሪስ ንግድ ኩባንያ ጠበቃ ነው ። በአስተሳሰቡ ጥብቅ አስተዋይ የሆነና ዕድሜውም በአርባዎቹ ውስጥ የሚገመት ነው ።

ካተሪን ስለኪርክ ሬኖልድስ ለኤቨሊን ስታወራ ፣ “ስለእርሱ ደስ የሚለኝ ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ? ቢትነቴ እንዲሰማኝ ያደርገኛል ። እንደዚያ ዓይነት ስሜት ሳይመጣብኝ ብዙ ጊዜ ሆኖታል” አለቻት።

“እንጃ” አለች ኤቨሊን ። “አንቺን ብሆን ጥንቃቄ አደርጋለሁ ። ለሁሉም ነገር አትቸኩዪ!”

“እሱስ አልቸኩልም” ብላ ካተሪን ቃል ገባችላት ።

ኪርክ ሬኖልድስ ካተሪንን በለንደን ውስጥ አንሸራሸራት ። ከመቶ ዓመታት በፊት የወንጀለኞች ጉዳይ ይታይበት ወደነበረው ጥንታዊ ግምብ በመሄድ ሰው ሰራሽ ፀጉርና የቡና ቤት አስተናባሪ ልብስ የለበሱ መልከ ጥፉ ሰዎችን እያለፉ በችሎቱ አዳራሽ ውስጥ ተንጐራደዱ ። በአሥራ ስምንተኛው መቶ ክፈለ ዘመን የተሠራውንም የኒውጌት ወህኒ ቤት ከውጭ ጐበኙ ። ከወህኒ ቤቱ ፊት ለፊት ሰፋ ብሎ የሚታየው መንገድ ብዙም ሳያስኬድ ጠበብ ብሎ ይታያል ።

“ይህ ያልተለመደ እንግዳ ነገር ነው” አለች ካተሪን ። “መንገዱን ለምን በዚህ ዓይነት እንደሠሩት ገርሞኛል ።”



“ሰፋ ያለው ብዙ ተመልካች እንዲይዝላቸው ታስቦ ነው ። የሞት ቅጣት የተፈረደባቸው ወንጀለኞች በሕዝብ ፊት የሚረሸኑት እዚሁ ሥፍራ ነው ።”

ካተሪን ደንገጥ አለች ። አባባሉ የእርሷንም ቁስል ነካካው ።

አንድ ቀን ምሽት ኪርክ ሬኖልድስ ካተሪንን በፒርስ አድርጐ ወደ ኢስት ኢንዲያዶክ ጐዳና ወሰዳት ።

“ከቅርብ ጊዜ በፊት እዚህ ላይ ፖሊሶች መንታ ሆነው ነበር የሚጓዙት” አላት ። “ወንጀለኞች የሚሰቀሉት እዚሁ ነው ።”

አካባቢው ጨለማና አስፈሪ ስለነበረ ካተሪን ስጋት አደረባት።

ከቴምስ ወንዝ ላይ በተሠራው የእንግሊዝ ጥንታዊ አነስተኛ የዊትቢ ሆቴል ፎቅ ላይ ሆነው ወደ ባሕር የሚገሰግሱትን መርከቦች እያለፉ ቁልቁል የሚበሩትን ጆልባዎች እየተመለከቱ እራታቸውን በሉ።

ካተሪን ከሌላ ሥፍራ ልዩነት ያላቸውን የለንደን ሆቴሎች ስያሜ ትወደዋለች ። በሌላ ምሽት ደግሞ በሲቲ ጐዳና ላይ የሚገኘውን ዘኢግል የተሰኘውን ውብ ሕንፃ ጐበኙ ።

“ሕፃን በነበርሽበት ወቅት ስለዚህ ሥፍራ መዝሙር ሳትዘምሪ እንዳልቀረሽ እርግጠኛ ነኝ” አላት ኪርክ ።

ካተሪን ትኩር ብላ አየችውና “መዘመር ቀርቶ ስለሥፍራውም ሰምቼ አላውቅም ።”

“ሰምተሻል እንጂ ። ዘኢግል የሚባለው ይህ ሥፍራ የድሮ የሕፃናት ግጥሞች ምንጭ ነው ።”

“የምን የሕፃናት ግጥም?”

ከብዙ ዓመታት በፊት የሲቲ ጐዳና የልብስ ሰፊዎች መናኸሪያ ነበር ። ቅዳሜና እሁድ ልብስ ሰፊዎች የገንዘብ እጥረት ስለሚያጋጥማቸው ካውያቸውንና ሌሎች የሥራ መሣሪያዎቻቸውን በአራጣ አስይዘው ደመወዛቸው ሲደርስ ያስለቅቃሉ ። ይህን በሚመለከት አንድ ሰው እንዲህ እንዲህ ሲል ግጥም ጽፎ ነበር —

“እላይ እታች በጐዳናው
ወጣ ገባ በኢግልም
እንዲያ ነበር ገንዘብ ሲሄድ

ካተሪን "ዊም ሁለት የሺህ ቤት ቁጥሮችን በሰላሣ ሴኮንድ ውስጥ አባዝቶ ማወቅ ይችላል ። ሃምሣ የስልክ ቁጥሮችን በአምስት ደቂቃ ውስጥ ሸምድዶ ሊይዝ ይችላል ። አንዴ በአእምሮው ውስጥ ከከተታቸው ደግሞ ጨርሶ አይረሳቸውም ።"

ኪርክ ሬኖልድስ ተገርሞ ዊም ቫንዲንን አተኩሮ ያየው ነበር።

"ቢሮዬ እንደአንተ ያለውን ሰው ሊገለገልበት ይፈልጋል።"

"እኔማ ሥራ ይገኝያለሁ" አለ ዊም ።

ኪርክ ሬኖልድስ ካተሪንን ወደ ቤቷ መልሶ ከመኪናው ስትወርድ "ስለ ቅዱስ ሞሪዝ አትረሺም አይደል?" ብሎ ጠየቃት ።

"የለም አይረሳኝም" አለችው መልሳ ። 'ግን ፤ ለምን ይረሳኛል ለማለት አቃተኝ?' አለች በሆዷ ።

ያንን ዕለት ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ዘግይቶ ስልክ ደወለላት ። ካተሪን ስለ ኪርክ ሬኖልድስ ልትነግረው ብላ ነበር ። በኋላ ግን ላለመንገር ወሰነች ።



# ምዕራፍ አሥር

## አቴንስ

ቄስ ኮንስታንቲኑን አንድ ነገር በጣም አድርጎ አሳስቧቸዋል። የፍሬደሪክ ስታቭሮስን በመኪና ተገጭቶ መሞትና የመኪናውንም ማምለጥ ዜና ከጋዜጣ ላይ ካነበቡ ጀምሮ ልባቸው በጣም ተሸብሯል። ቄሱ የክህነት ሥልጣን ከተቀበሉ አንስቶ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኑዛዜዎችን ተቀብለዋል ፤ ግን የፍሬደሪክ ስታቭሮስ ኑዛዜ የማይሽር የኅሊና ቁስል አድርሶባቸዋል ።

"የሚያሳስብዎት ምንድን ነው?" ሲላቸው ቄስ ኮንስታንቲን ዞር ብለው ከቤታቸው ውስጥ ተቀምጦ የነበረውን መልከ መልካም ወጣት አዩትና "ምንም የኔ ወዳጅ" ብለው መልስ ሰጡ ።

"ታዲያ ምን ነካዎት ?"

"በጣም አዝናለሁ አንድ የንስሐ ልጄ በአውቶሞቢል አደጋ በመሞቱ ነው ።"

"ሞትማ ለሁላችንም አይቀር ።"

"አዎ ፤ ቢሆንም ሰውዬው በጣም የተጨነቀ ሰው ነበረ ።"

"ማለት አዕምሮው ተቃውሷል ነው የሚሉት?"

"አይ ፤ አንድ ጥብቅ ምስጢር ነበረው ። ይህንኑ አምቆ ይዞ ለማቆየት ተቸግሮ ነው ።"

"ምን ዓይነት ምስጢር?"

ቄሱ ኮስተር ብለው ወደ ወጣቱ ዞሩና "ታውቃለህ አይደል? በንስሐ መልክ የተነገረኝን ምስጢር ሌላ ቦታ ማባከን የለብኝም ።"

"አይ ከእኔ የሚደብቁት ምስጢር የለም ብዬ ነው ።"

"እርሱማ የለም ፤ ጂኦርጂኦስ ፤ ግን ..."

"ያም ሆነ ይህ ሰውዬው ሞቷል ። ታዲያ ምስጢሩን መደበቅ ምን ለውጥ ያመጣል?"

"ምንም ፤ የእኔ ግምት ግን..." አሉና በመጨረሻ ነገሩን ዘርዝረው ለጂኦርጂኦስ ላቶ አጫወቱት ።

ጂኦርጂኦስ ላቶ የተወለደው በአቴንስ ከተማ ውስጥ ቆሻሻማ
አካባቢ ነው ተብሎ ከሚታወቀው ሠፈር ውስጥ ነው ። ዕድሜው
አሥራ ሁለት ሲሆነው የለየለት ዱርዬ ሆነ ። በመጀመሪያ በአቴንስ
ጐዳናዎች ላይ እየተዘዋወረ መጠጥ በመሸጥ ፣ ለቱሪስቶችም ልዩ
ልዩ አገልግሎት በማበርከት ገንዘብ ያገኝ ነበር ። ጠየም ያለው
ፊቱና ፈርጠም ያለ ሰውነቱ ለመላ አካሉ ውበትን ሰጥቶታል ።

የላቶ ኑሮ የተለወጠው የስፒሮስ ላምብሩ ረዳት ከሆነው ኒኮስ
ቬሪቶስ ጋር ከተዋወቀ በኋላ ነው ። ሁለቱ ሰዎች በወዳጅነት ብዙ
ጊዜ ከቆዩ በኋላ ቬሪቶስ ላቶን በላምብሩ ድርጅት ውስጥ አስቀጠ
ረው ። በመጀመሪያ ጂኦርጂኦስ ላቶ ጥያቄውን ለመቀበል ፈቃደኛ
ባይሆንም በኋላ ተስማምቶ ሥራውን ጀመረ ። በኩባንያው ውስጥ
መሥራቱ ደስታን እየሰጠው መጣ ። የኩባንያው ፖስታና መልእ
ክት አመላላሽ ሆኖ መሥራቱ ሌሎች ሰዎችን እንዲተዋወቅና ተጨ
ማሪ የጉርሻ ገንዘብም እንዲያገኝ ረድቶታል ። ቄስ ኮንስታንቲንንም
የተዋወቃቸው ያኔ ነበር ።

ጂኦርጂኦስ ላቶ ያን ዕለት ከሰዓት ከቄስ ኮንስታንቲኑ ቤት
ከወጣ በኋላ በአእምሮው ውስጥ ብዙ ነገር መመላለስ ጀመረ ። ቄሱ
የነገሩት ምስጢር በጣም ተፈላጊና ጠቃሚ ዜና ነው ። ከዚህም እን
ዴት አድርጐ ገንዘብ ማግኘት እንደሚችል ያወጣ ያወርድ ጀመረ ።
'ለኒኮስ ቬሪቶስ ብነግረው ደስ ይለው ነበር ።' ግን ከዚህ የተሻለ
እቅድም መጣለት ። 'ዜናውን ይዤ በቀጥታ ወደትልቁ አለቃ እሄዳ
ለሁ' አለ ላቶ ለእራሱ ። 'ጥሩው ገንዘብ የሚገኘውም ከዚያው
ነው ።'

በሚቀጥለው ቀን ላቶ ወደ ስፒሮስ ላምብሩ ፀሐፊ ቢሮ ገባ ።
መቀመጫዋ ላይ የነበረችው ፀሐፊ ቀና አለችና "እሃ፣ ዛሬስ
ፖስታው ቶሎ መጣ ጂኦርጂኦስ" ብላ ተናገረች ።

ጂኦርጂኦስ ላቶ ጭንቅላቱን ነቀነቀና "አይደለም እመቤቴ ፤
ሚስተር ላምብሩን ማነጋገር ፈልጌ ነው" አላት ።

ፈገግ አለችና "የምርህን፣ ስለምን ጉዳይ ልታነጋግረው ፈልገህ
ነው? ስለሥራ ጉዳይ የምታቀርበው አሳብ አለህ?" አለች በምፀት
አነጋገር።

ላቶ ኮስተር አለና "አይደለም ፣ ከምትዪው ጋር ግንኙነት የለ



ውም ። እናቴ ልትሞት መቃረቧን ሰማሁ ። ስለዚህ እኔ...እኔ ወደዚ
ያው መሄድ አለብኝ ። ሚስተር ላምብሩ እዚህ ቀጥሮ ያሠራኝ ስለነ
በረ ላመሰግነው ነው ። ከአንድ ደቂቃ በላይ ጊዜ አልወስድም ።
ግን ሥራ ከበዛበት..." ብሎ ወደ ኋላ ዞር ብሎ ለመሄድ ተነሳ ።

"ቆይ ፣ ቅር የሚለው አይመስለኝም ።"

ከአሥር ደቂቃዎች በኋላ ጂኦርጂኦስ ላቶ ከስፒሮስ ላምብሩ
ቢሮ ውስጥ ቆሞ ነበር ። እዚህ ቢሮ ውስጥ ከዚህ ቀደም ገብቶ አያ
ውቅም ። የቢሮው ውበትና ምቾት በጣም አስደነቀው ።

"መልካም ፣ አንተ ወጣት እናትህ ልትሞት መቃረቧን በመስ
ማቴ በጣም አዘንኩ ። ምናልባት ጥቂት ጉርሻ..."

"አመሰግናለሁ ጌታዬ ። እዚህ የመጣሁበት ምክንያት በእር
ግጥ ይህ አይደለም ።"

ላምብሩ ግንባሩን ኮስተር አደረገና "አልገባኝም" አለው ።

"ሚስተር ላምብሩ አንተን በጣም ይጠቅምሃል ብዬ የማስበው
ተፈላጊ ወሬ አለኝ ።"

በጣም የመጓጓት ዓይነት ገጽታ ከላምብሩ ፊት ላይ ይነበብ ነበር ።
"እሃ ፣ እውነትህን ነው? አሁን ትንሽ ሥራ የበዛብኝ መሰለኝ ። ምናል
ባት ..."

"ስለኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነው!" አለና እቅጩን አፈረጠ ።
"በጣም ወዳጄ የሆኑ አንድ ቄስ አሉ ። ወዲያውኑ በመኪና አደጋ
የተገደለ አንድ ሰው ኑዛዜውን አሰምቷቸው ነበር ። ለሰውዬው ነግ
ሯቸው የነበረው ስለኮንስታንቲን ዴሚሪስ ነው ። ሚስተር ዴሚሪስ
በጣም አሰቃቂ ነገር ነው የሚሠራው ። በእውነት በጣም የሚዘግ
ንን። በዚህም ጥፋቱ ወህኒ ሊወርድ ይችላል ። ግን አንተ ለመስ
ማት የማትፈልግ ከሆነ..."

ስፒሮስ ላምብሩ ነገሩን ለመስማት በጣም ጓጓና "ቁጭ በል
...ስምህ ማነው?" አለው ።

"ላቶ ጌታዬ ፣ ጂኦርጂኦስ ላቶ ።"

"መልካም ፣ ላቶ ፣ እስቲ ከመጀመሪያው ጀምር ..."

የኮንስታንቲን ዴሚሪስና የሜሊና ትዳር ለብዙ ዓመታት የጭ
ቅጭቅ መድረክ ነበር ። ሆኖም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በመሐላ
ቸው ድብድብ ታይቶ አያውቅም ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የሜሊናን የቅርብ ጓደኛ በማውጣቱ ባልና ሚስቱን ከባሰ ብጥብጥ ላይ አድርሷል ።

"ያየሃትን ሴት ሁሉ አትምርም ማለት ነው" አለች ሜሊና በጩኸት "ሁሉንም ካልነካካህ ሞትህ ነው።"

"ይህን ክፍት አፍሺን ብትዘጊ ይሻልሻል ።"

"አፌን ልታዘጋኝ አትችልም" አለች ሜሊና በድፍረት ። "ምን ዓይነት ቅሌታም ሴሰኛ እንደሆንክ ለመላው ዓለም ላሳውቅ ነው ። ወንድሜ እውነቱን ነበር ። ተወዳዳሪ የሌለህ አረመኔ ነህ ።"

ዴሚሪስ ፊቷ ላይ በጥፊ ሲመታት ከክፍሉ ወጥታ ሮጠች ።

በሚቀጥለው ሳምንት ሌላ ጭቅጭቅ በመካከላቸው ተነሳና አሁንም እንደገና መታት ። ሜሊና ሻንጣዋን ይዛ የወንድሟ የግል ደሴት ወደሆነችው አቲኮስ በአውሮፕላን በረረች ። እዚያም ልቧ በጣም ተሰብሮ ብቻዋን ለአንድ ሳምንት ያህል ቆየች ። ቧኗ ናፈቃትና ለጥፋቱ የይቅርታ ምክንያት በአእምሮዋ ውስጥ መደርደር ጀመረች ።

'ጥፋቱ የእራሴ ነው' አለች ሜሊና በአሳቧ ። 'ኮስታን ማናደድ አልነበረብኝም ። የመታኝ በጣም ስለተናደደ እራሱን መቆጣጠር አቅቶት ነው ። ኮስታ በጣም ባይወደኝ ኖሮ አይመታኝም ነበር።'

እነኚህን የይቅርታ ምክንያቶች የምትደረድረው ትዳሯን ላለማፍረስ መሆኑን ሜሊና ወደ ኋላ ተረድታለች ። በሚቀጥለው እሁድ ወደ ቤቷ ተመለሰች ።

ዴሚሪስ ቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ ተቀምጧል ።

ሜሊና ስትገባ ቀና ብሎ ተመለከታትና "እና ልትመለሺ ወሰንሽ?" አላት ።

"ይህኮ ቤቴ ነው ኮስታ ። አንተ ባለቤቴ ነህ ፤ ደግሞም እወድሃለሁ ። ግን አንድ ነገር ልንገርህ ። ሁለተኛ ጫፌን ከነካህ እገድልሃለሁ ።"

ዓይኗን ትኩር ብሎ ሲያይ የምሯን መሆኑ ታወቀው ።

ከዚያ በኋላ የጋብቻ ግንኙነታቸው በመጠኑ የተሻሻለ ይመስል ነበር ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስም ከንዴት እራሱን መቆጣጠር ከጀመረ ሰንበት ብሏል ። ከሌሎች ጋር መማገጡን ግን አላቆመም ።



ሜሊናም ይህንን ርኩስ ተግባሩን እንዲያቆም መጫኗን ተወች ። 'ጋለሞታዎቹን ሁሉ የሚሰለችበት ቀን ይመጣል' አለች በአሳቧ። 'እኔ ብቻ እንደምበቃው የሚገነዘብበት ቀን ይመጣል ።'

ቅዳሜ ዕለት ምሽት ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ወደ ውጭ ለመውጣት የእራት ኮት ሲለብስ ሜሊና ፣ ወደ ክፍሉ ገባች ።

"የት ልትሄድ ነው?"

"ቀጠሮ አለኝ"

"ረሳህ እንዴ? ዛሬ ማታኮ ስፒሮስ ዘንድ እራት ተጋብዘናል።"

"አልረሳሁም ። ግን ከሱ የበለጠ ነገር አጋጥሞኝ ነው ።"

ሜሊና በንዴት ቆማ አየችው። "ምን እንደሆነ እንኳ አውቀዋለሁ ። ወደ ጋለሞታህ ልትሄድ ነው አይደል?"

"ምላስሽን ብትሰበስቢው ይሻላል ። ጨቅጫቃ ሚስት እየሆንሽ ነው ሜሊና" አለና በመስተዋቱ ውስጥ እራሱን መመልከት ጀመረ ።

"እንዲህ ስትሆን ዝም ብዬ አላይህም!" በሷ ላይ የሚፈፅመው በደል አልበቃ ብሎት ወንድሟን በግልፅ መስደቡ አሳርሯታል ። ስለዚህ እሱን የምትጐዳበት መንገድ ማግኘት ነበረባት ። አንድ መንገድ ብቻ ነው ያላት ። "ዛሬ ማታ ሁለታችንም እቤት መቆየት አለብን" አለችው ሜሊና ።

"እውነትሽን ነው?" አለ በሽሙጥ አነጋገር ። "እኮ ለምን?"

"ዛሬ ቀኑ ምን እንደሆነ አታውቅም ?" ብላ ሳቀችበት ።

"አላውቅም ።"

"ልጅህን የገደልኩበት መታሰቢያ ቀን ነው ኮስታ ። ራሴ አስወጥቼው ነው ።"

ክው አለ ። የዓይኑ ብሌን ቀለም የበለጠ ሲጠቁር ታያት ።

"ካንተ ሌላ ልጅ በማኅፀኔ ለመቋጠር ስላልፈለግኩም ነበር ዶክተሮቹ ማኅፀኔን እንዲዘጉት ያደረግሁኝ" ስትል ዋሸች ።

እራሱን መቆጣጠር አቃተው ። በጥፊ መታት ፣ ቀጥሎም ይቀጠቅጣት ጀመር ። ሜሊና እየጮኸች እምልጣው ወደሳሎኑ ሮጠች። ዴሚሪስ ተከተላት ። ከሳሎኑ መውጫ ላይ ስትደርስ ከኋላ ያዛት ።

"ስለዚህ ሥራሽ እገድልሻለሁ" ሲል እንቧረቀባት ። እንደገና ሲመታት ሜሊና ኅሊናዋን ስታ ከደረጃው ተንከባላ ወደቀች ።

ብድቧል ። እርሷን ግን ሴት መነኩሴዎች ደብቀዋት በሕይወቷ ትገኛለች ።

እና ፣ ላምብሩ እንዴት አድርጐ ኮንስታንቲን ዴሚሪስን እንደሚያጠፋ አሁን ተገንዝቧል ።

'ቶኒ ሪዞሊ ።'



# ምዕራፍ አሥራ አንድ

የቶኒ ሪዞሊ ችግሮች ተበራክተዋል ። ሁሉም ነገር እየተበላሸበት ነው ። ለተፈጸመው ነገር ተጠያቂ ባይሆንም ሸሪኮቹ እሱ ላይ እንደሚያላክኩ ያውቃል ፣ ሰዎቹ ምክንያትና ሰበብ የሚቀበሉ አይደሉም።

ጉዳዩን ይበልጥ አሳሳቢ ያደረገው ነገር ቢኖር የአደንዛዥ ዕፅ አጓጓዝ የመጀመሪያ ደረጃ ሥራ በተሳካ ሁኔታ መፈጸሙ ነው ። አደንዛዥ ዕፅን ደብቆ አቴንስ ውስጥ ያለ እንቅፋት በማስረግ በጊዜያዊነት ከአንድ መጋዘን ውስጥ አከማችቶታል ። ከአቴንስ ወደኒውዮርክ ለሚበር አውሮፕላን አስተናጋጅ ጉቦ ሰጥቶ ዕቃውን በሥውር ሊያወጣ ተዘጋጅቶ ነበር ። በረራው ከመጀመሩ ከሃያ አራት ሰዓት በፊት አስተናጋጁ ሰክሮ መኪና ሲያሽከረክር ተይዞ ታሰረና ከሥራውም ተባረረ ።

ቶኒ ሪዞሊ ሌላ አማራጭ ዘዴ መፈለግ ነበረበት ። ልጇን ለመጠየቅ ወደአቴንስ መጥታ የነበረችው የሰባ ዓመት አሮጊት ሣራ ሙርቺሰን ሻንጣውን ይዛለት ወደ ኒውዮርክ እንድትሄድ ጠየቃት ። አሮጊቷ በሻንጣው ውስጥ ስለነበረው ነገር ምንም የምታውቀው የላትም ።

"ለእናቴ ለመላክ ቃል ገብቼላት የነበር ስጦታ ነው" አለና ቶኒ ሪዞሊ አስረዳት ። "ይህንን ዕቃ ለማድረስ ታማኝ ነሽ ብዬ ስለገመትኩ ከዚህ ወደኒውዮርክ የሚያደርስ የአውሮፕላን ትኬት ልቆርጥልሽ እስቤአለሁ ።"

"ግድ የለም ይህማ ጨርሶ አያስፈልግም" ብላ ተቃውሞዋን ለመግለጽ ሞከረች። "እንዲሁ በነፃ ባደርስልህ ደስ ይለኛል ። ከእናትህ መኖሪያ የእኔም ቤት ብዙ አይርቅም ። ልተዋወቃት እኔም እፈልጋለሁ ።"

"እርግጠኛ ነኝ እርሷም ብታገኝሽ ደስ ይላት ነበር" አላት ቶኒ ሪዞሊ በብልጠት ። "ችግሩ እርሷም በሽተኛ ናት ። ሆኖም ሻንጣውን የሚቀበልሽ ሰው ይኖራል ።"

አሮጊቷ ለሥራው በጣም የምትስማማ ናት ። ደስ የምትል አሜሪካዊት አያት። የጉምሩክ ሠራተኞችም ቢሆኑ እንዲያ ዓይነቷ